Daniel Fikadu Law Office

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

ቀን/Date ግንቦት 30 2015
ቁጥር/ Ref. No. መ/ፌ-2ዓ/44308

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች
ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ምክንያት ሳይገለጽ የሚሰጥን ውሳኔ/ትዕዛዝን ይመለከታል

ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የሚያዩዋቸውን ጉዳዩች መልስ ሰጭን አያስቀርብም በማለት ሲዘጉ አስቀድሞ በተዘጋጀ ቅጽ በመጠቀም ምክንያት ሳያሰፍሩ መዝገቡን የሚዘጉበት አሰራር ተዘርግቶ ለረጅም ጊዜ ሲተገበር ቆይቶዋል። ይህ አሰራር በባለጉዳዩች በተለይ ይግባኝ ባዩች በኩል ከፍተኛ የቅሬታ ምንጭ ሆኖ ይታያል። በሌላ በኩል ጉዳዩች እልባት እንዲያገኙ ስለሚረዳ ዳኞች ከስር ፍርድ ቤት አቋም ጋር በሚስማሙበት ጊዜ ተመሳሳይ ምክንያት በመጻፍ የሚያጠፉትን ጊዜ በመቀነስ ውጤታማነትን ያረጋግጣል የሚል ክርክርም ይቀርባል። እስከ አሁን ባለው አሰራር በርካታ መዝገቦችን በአጭር ጊዜ ለመወሰን የተቻለ ቢሆንም የባለጉዳዩች ቅሬታ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና የፍርድ ቤቱን መታመን እየሸረሸረው በመሄድ ላይ ነው። ለዚህም በቅጽ መዘጋቱን በመቃወም በተደጋጋሚ በዳኞች ላይ የሚቀርቡት የዲስፕሊን አቤቱታዎች እና በየመድረኩ የሚነሱ ቅሬታዎች ማሳያ ሆነው መወሰድ ይችላሉ። ይህም የመዝገቦቹ መዘጋት ከጎብረተሰቡ የፍትሕ ግንዛቤም ሆነ መረዳት ጋር የሚጋጭ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በዘጋቸው መዝገቦች ልክ እርካታን ማረጋገጥ ላለመቻሉ ዋቢ ሆኖ የሚጠቀስ ነው። ስለዚህ ይህን አሰራር መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶዋል።

መዝገቦችን ቅጽ በመሙላት መዝጋትን ቅቡል ለማድረግ የሚቀርበው ብቸኛው ምክንያት ፍጥነት ነው። ይህን ተከተሎ የሚቀርበው ድጋፍ መዝገቡ የሚዘጋበት ምክንያት በስር ፍርድ ቤት የተገለጸ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ችሎት መዝገቡን ሲዘጋ የስር የፍርድ ቤትን ምክንያት ተቀብሎ ስለሆነ ተጨማሪ ገለጻ አያስፈልግም የሚል ክርክር ነው። ይህ ክርክር ተወሰኑ ጉዳዩች እውነት ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ቢኖርም በሁሉም ጉዳዩች የሚሰራ ምክንያት አድርጎ መውሰድ ተገቢ አይሆንም። ለምሳሌ የስር ፍርድ ቤት

ስልክ/Tel. +251 111 553400
ፋክስ/Fax +251 111 550278
ፖ.ሳ.ቁ/P.O.Box 6166

ተገቢውን ጭብጥ አልያዘም ወይም ያልመረመረው ማስረጃ ወይም ያልሰማው ምስክር ወይም ተፈጻሚ ያላደረገው ሕግ አለ ወይም አግባብነት የሌለው ሕግ ተጠቅሞዋል ወ.ዘ.ተ. የሚሉ አቤቱታዎች የቀረበለት ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ምንም ባላለበት ነጥብ ላይ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ምክንያት ተቀብሎዋል ሊባል አይችልም። ስለዚህ የሚቀርበው ምክንያት በራሱ መመዘን ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍጹም እውነት ተደርጎ መወሰድ የሚችል አይደለም። ከዚህም በላይ ግን ከዚህ አሰራር በመቃረን የሚቀርቡት ምክንያቶች አሰራሩ የሚደርሰው ጉዳት ከሚገኘው ጥቅም የበለጠ ለመሆኑ ማሳያ ሆነው መቅረብ ይችላሉ።

ምክንያት ሳይገለጽ የሚሰጥ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በብዙ ምክንያቶች ስህተት ለመሆኑ አስረጅ የሚቀርብበት ሲሆን የተወሰኑትን መጥቀስ ይቻላል። የተፈጥሮ ፍትሕ መርህ (principles of natural justice) ተደርገው ከሚወሰዱት ውስጥ ለውሳኔ ወይም ትህዛዝ ምክንያት መስጠት አንዱ ሲሆን ይህም ከተሰጠው ውሳኔ ይዘት መረጋገጥ ስላለበት የሚሰጡ ውሳኔዎች ምክንያት መያዛቸው ሰዎች ስለፍትህ ሲያስቡ ከሚጠብቋቸው ውጤቶች አንዱ ነው። ዳኞች ከየትኛውም ሙያ በላይ እንዲሁም ካለባቸው ሕዝባዊ ኃላፊነትና ከተሰጣቸው ነጻነት አንጻር ምክንያታዊ መሆን የሚጠበቅባቸው ከመሆኑም በላይ ዳኝነትም የሚመሰረተው በምክንያት ላይ ስለሆነ ይህ አላባ ሲጠፋ የዳኝነት ስራን ጥያቄ ውስጥ ይከትታል። ሌላው ነጥብ ምክንያት መስጠት የግልጽነትና የተጠያቂነት ዋስትና ነው። ዳኞች በሚወስኑት መዝገብ ምክንያታቸውን ካላሰፈሩ ለባለጉዳዩ ምላሽ እየሰጡ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን በሚቀርብባቸው አቤቱታ ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም። ይግባኝ ባይ ጉዳዩ እንደታየለት ማረጋገጥ አይችልም፣ የዳኝነት ተቋማትም ተጠያቂነት ማስፈን አይችሉም። ሌሎች ባለድርሻ አካላት ምን እንደተከሰተ ማወቅ ስለማይችሉ አሰራሩ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያጠፋል። ምክንያት የመስጠት አሰራር ዳኞችም ራሳቸው በራሳቸው ዲሲፕሊን ለማድረግ ስለሚረዳቸው የውሳኔን ጥራት እንዲኖር ያደርጋል ወይም ውሳኔዎች በዘፈቀደ የሚሰጡበትን አጋጣሚ ያጠፋል።

መልስ ሰጭን ሳይጠራ ፍርድ ቤቱ ይግባኝን የሚሰርዝበትን ሥነ ሥርዓትን የሚደነግገው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ ጉድለት የሌለበት መሆኑን ከተረዳው መልስ ሰጭን ሳይጠራ ይግባኙን ሰምቶ አቤት ባዩን ሊያሰናብት እንደሚችል ይደነግጋል። ከድንጋጌው ይዘት መረዳት የሚቻለው የመዝገቡ ግልባጭ እንደሚመረመር እና የቃል ክርክር ሂደት እንደሚከናወን ሲሆን የዚህ ሂደት ውጤት ደግሞ ፍርድ ለሚለው ቃል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 3 ስር የተሰጠው ትርጉም እና በአንቀጽ 182 የፍርድ ይዘት

ምን እንደሆነ ከተጠቀሰው ዝርዝር አንጻር መዝገብ በውሳኔም ሆነ በትህዛዝ ሲዘጋ ምክንያት መጥቀስ አስፈላጊ መሆኑ ሚዛን የሚደፋ ድምዳሜ መሆኑን መረዳት አያዳግትም።

ምክንያት ባለመስጠት የሚገኝ ፍጥነትና ምክንያት በመስጠት የሚገኝ ጥቅም መካከል ያለውን ውጥረት የተለያዩ የሕግ ግዛቶች የተለያየ አቋም የሚይዙበት ሲሆን ሚዛን መጠበቅ የግድ አስፈላጊ መሆኑ የሚያስማማ ድምዳሜ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የዳኞች ቁጥርና የመዝገብ ብዛት ግምት ውስጥ በማስገባት ዳኞች ምክንያት ሳይሰጡ የሚሰሩበትን አሰራር በመቀየር ለሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎች በቀረበው የይግባኝ መነሻ ተገቢውን ምክንያት በአጭሩ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በዝርዝር ለመግለጽ እንዲያስችል ሲጠቀሙበት የነበረውን ቅጽ ማሻሻል ያስፈልጋል። ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ይህን ቅጽ ሲጠቀሙ ምክንያት መጥቀስን ተግባራዊ ማድረግ ለተገልጋዩ ቅሬታ ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም የፍርድ ቤቱን ተዓማኒነት መጨመር ይጠበቅባቸዋል።

ስለዚህ ከሰኔ 7 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ሌላኛው ተከራካሪ ወገን መጥራት ሳይስፈልግ መዝገብ በሚዘጉበት ጊዜ ምክንያት መጥቀስ ያለባቸው በመሆኑ ሁሉም የይግባኝ ችሎቶች ይህን ተግባራዊ እንዲያደርጉ፤ ሁሉም ፍርድ ቤቶች ከተጠቀሰው ቀን በኋላ የሚቀርብ የይግባኝ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 327 እና 328 የተመለከተውን ይዘት እንዳለው ማረጋገጥና የይግባኝ ቅሬታዎች በተራ ቁጥር እና በርዕስ ተለይተው መመልከታቸውን ለማረጋገጥ በሁሉም በኩል ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ እና ባለጉዳዮችም ስለአሰራሩ ግንዛቤ የሚያገኙበትን መንገድም እንዲፈጥሩ እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>:-

- ለክቡር ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
- ለክብርት ምክትል ፕሬዝደንት ጽ/ቤት
- ለፕሬዝደንት ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለም/ፕሬዝደንት ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለዋና ሬጅስትራር
- ለዳኝነት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ለጉዳዮች ፍሰት አስ/ዳ/ዳይሬክተር

<u>ፌ/ጠ/ፍ/ቤት</u>

- ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>